# ጥምረት ለነጻነት ለእኩልነትና ለፍትህ በኢትዮጵያ

www.timret.org

## የምስረታ ሰነድ

**እኛ ስማችን ከዚህ ሰነድ መጨረሻ የተዘረዘረው የፖለቲካ ሃይሎች**

በኢትዮጵያ ውስጥ የዘረኛው የወያኔ አገዛዝ የስልጣን እድሜ መራዘም፣ የሃገራችንን ብሄራዊ ጥቅምና ደህንነት የበለጠ የሚጎዳ ህዝብን የበለጠ ለስቃይና ለውርደት የሚዳርግ መሆኑን በመገንዘብና ይህንን አስከፊ ሂደት ማስቆም ጊዜ የሚሰጠው ጉዳይ አለመሆኑን በመረዳት፣

የኢትዮጵያ ህዝብ የራሱንና የሃገሩን ቸግሮች የሚያወሳስበውን የወያኔ ዘረኛን አምባገነናዊ አገዛዝ በተናጠል የሚታገሉ ድርጅቶች አቅማቸውንና ጥረታቸውን አስተባብረው በግፍና መከራ አምራቹ አገዛዝ ላይ በጋራ እንዲነሱ ያለውን ጥብቅ ፍላጎት ግምት ውስጥ በማስገባት፣

የ 2002 የወያኔ ምርጫ ተውኔት የኢትዮጵያ ህዝብ በአንድ ዘረኛ፣ ፍጹም እምባገነናዊና አዋራጅ አገዛዝ ስር መውደቁን ከመቼውም በላይ ገሃድ ያደረገው መሆኑንና ይህንንም መከራና ውርደት ማስቆም የሚቻለው፤ በተቀናጀ፣ ህዝባዊ ሃይልና መራራ ትግል ይህን ዘረኛ አምባገነናዊ ሃይል በሁሉም አቅጣጫና በሁሉም አይነት የትግል ስልት ወጥሮ በማንበርከክ ብቻ እንደሆነ በማመን፣

መሰረተ ሰፊ የሆነና ሁሉን አቀፍ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ህብረት ምስረታ፣ ዘረኛውንና አምባገነናዊ የሆነውን የወያኔ አገዛዝ ማስወገጃ፣ ዘለቄታነት ያለው ሰላም ማስፈኛ፣ የሁሉም አይነት መብቶች፣

ነጻነቶች፣ የብሄራዊ አንድነትና ጥቅም ማስከበሪያ፣ የኢኮኖሚ እድገትና ማህበራዊ ፍትህ መቀዳጃ ፍቱን መሳሪያ መሆኑንም ከልብ በመቀበል፣

ይህ የሶስት ድርጅቶች ጥምረት ጅማሮ ወደ ሰፊና ሁሉን አቀፍ ህብረት የሚወስደን አንድ እርምጃ መሆኑን ከምር በማመን፣

ለሰፊና ሁሉን አቀፍ ህብረት ምስረታ ተግተን እንደምንሰራ ለህዝብ ቃል በመግባትና ለዚህም አጣዳፊ የመተባበር ተግባር ሁሉም የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ታጋይ ሃይሎች ተግተው እንዲሰሩ ጥሪያችንን በማቅረብ ፡፤

*__ጥምረት ለነጻነት ለእኩልነትና ለፍትህ በኢትዮጵያ Alliance for Liberty, Equality, and Justice in Ethiopia (ALEJE)__ ተብሎ የሚራውን የፖለቲካ ጥምረት መስርተን ትግላችንን በጋራ ለማካሄድ ተስማምተናል።*

## *__ምእራፍ1፥ የጥምረቱ አባል ድርጅቶች የሚጋሩዋቸው መሰረታዊ እሴቶች__*

1. ዛሬ በሃገራችን ውስጥ የሰፈነው አምባገነናዊ አገዛዝ እንዲያከትምና በቦታው በሁሉም አስተዳደራዊ እርከኖች ስልጣን በህዝብ ዴሞክራሲያዊ ፍላጎት ብቻ የሚወሰን መሆኑን፣
2. በጥምረቱ ውስጥ የሚሳተፉ ድርጅቶች የፖለቲካ ስልጣን ዴሞክራሲያዊ በሆነ ሂደት ብቻ የሚያዝና የድርጅቶቹ ዋና የትብብር አላማ ዴሞክራሲያዊ የስልጣን ሽግግርን ማመቻቸት መሆኑን፣
3. የጥምረቱ አባል ድርጅቶች ህዝብ በሃቀኛ የዴሞከራሲ ሂደት የሚወስናቸው ማናቸውንም ዴሞከራሲያዊ ውሳኔዎች በጸጋ የሚቀበሉ መሆናቸው፣
4. ህዝብ የገዛ ህይወቱን በሚመለከት ጉዳዮች ላይ መወሰን እንዲችል መንግስታዊ ስልጣንና አስተዳደር ባልተማእከለ መንገድ ህዝብ ተሰባስቦ እስከሚኖርባቸው ዝቅተኛ የአስተዳደር እርከኞች ድረስ መውረድ የሚገባው እንደሆነ፣ የህግ የበላይነት የሰፈነበት እያንዳንዱ ዜጋ በህግ ፊት እኩል እንደሆነ፣ መሰረታዊ ነጻነቶችና መብቶች ለሁሉም የሚከበሩ መሆኑን፣

5. ከእዚህ በላይ የተዘረዘሩት መሰረታዊ የጋራ እሴቶች በግለሰብ ዜጋ ደረጃ ሆነ፣ ዜጎች በቡድን በተሰባሰቡባቸው ሁኔታዎች እንዲከበሩ፣ ከማንኛውም የፖለቲካ ሆነ ሌላ ቡድን ነጻና ገለልተኛ የሆኑ የዴሞክራሲ መብቶችና የነጻነት ማስከበሪያና ዋስትና የሚሆኑ ነጻ ተቋማት መመስረት አስፈላጊ መሆኑን፣
6. በጥምረቱ አባል ድርጅቶች መሃል የሚነሱ መሰረታዊ የፖሊሲ ልዩነቶች፣ በኢኮኖሚ፣በማህበራዊ፣ በዲፕሎማሲያዊና እንዲሁም በሌሎቸ ዘርፎች በሙሉ፣ ህዝብ መሰረታዊ የዲሞከራሲ መብቶቹ በሚከበሩበት ወቅት ፍርዱን የሚሰጥባቸው እንደሚሆኑና እስከዛው ድረስ እነዚህ ልዩነቶች የጥምረቱን የጋራ ጥረቶች ሊያውኩ የማይገባ መሆኑን፣
7. ጥምረቱ ለራሱ ስራ ሆነ ወይም ከህዝብ ጋር በሚኖርው ግንኙነት ከፍተኛ የሆነ የተጠያቂነትና የግልጽነት አሰራር የሚከተል መሆኑን፣
8. በቀን ከቀን የጥምረቱ አባል ድርጅቶች የስራ እንቅስቃሴ ውስጥ የሚነሱ ማናቸውም ልዩነቶች የጋራ ስምምነት ለመፍጠር በሚያስችል ግልጽና ዴሞክራሲያዊ ውይይት ለመፍታት ጥረት የሚደረግ መሆኑን የጋራ ስምምነት ላይ መድረስ የማይቻል ከሆነ ውሳኔ በጥምረቱ ህገ ደንብ አማካይነት የሚወሰን እንደሆነ፣

## *ምእራፍ 2፦ የጥምረቱ መሰረታዊ ዓላማዎች*

1. የወያኔ/ኢህአዴግ ዘረኛና አምባገነናዊ አገዛዝን በተቀናጀ ሁለገብ ትግል በማስወገድ፣
2. ሁሉም የፖለቲካ ኃይሎች የሚሳተፉበት ብሔራዊ ጉባኤ መጥራት ፤
3. በዚህ ጉባኤ ውሳኔ መሰረት ዴሞክራሲያዊ የሽግግር መንግስት መመስረት፡
4. በሽግግሩ ወቅት ለዴሞክራሲያዊ ምርጫ አስፈላጊ የሚሆኑ ቅድመ ሁኔታዎችን ማመቻቸትና ነፃና ፍትሃዊ አገራዊ ምርጫ እንዲካሄድ ማድረግ።

## ምእራፍ 3፥ የጥምረቱ መሰረታዊ የፖለቲካ መርሆዎች

1. በአገሪቱ ውስጥ የመንግሥት ስልጣን በነፃና ፍትሃዊ የሕዝብ ምርጫ ብቻ የሚመጣና ተግባራዊ የሚሆን መሆኑን መቀበል፣
2. በህዝቦችዋ ዕኩልነት፣ ፍትህና የጋራ ራዕይ ላይ የተመሰረተ የኢትዮጵያን አንድነት መቀበልና ለዚሁ ተግቶ መሥራት፣
3. የፖለቲካ ልዩነቶች እና ማናቸውም ብሄራዊ ጉዳዮች በሰላማዊ የፖለቲካ ውይይትና፣ በስምምነት ወይም በሕዝብ ውሳኔ ብቻ የሚፈቱ መሆኑን መቀበል ናቸው።

## ምእራፍ 4፥ የጥምረቱ ተግባሮች

1. ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ዓላማዎችና መርሆዎች ተግባራዊ ለማደረግ ጥምረቱ እንደ አንድ ወጥ ድርጅት በመሆን ይንቀሳቀሳል፤ ለብሔራዊ አንድነት፣ ለእኩልነት ለፍትህና ለዴሞክ ሁለገብ ትግል ማድረግ፣
2. ለሁለገብ ትግሉ መሳካት አጠቃላይ ስትራትቴጂ፣ ታክቲክና የተግባር መርሃ ግብሮችንና ግቦችን መቀየስ፣ መወሰንና ተግባራዊ ማድረግ፤
3. የጥምረቱን በጀት ማዘጋጀት፤ አስፈላጊ የሆነውን ገንዘብ ከንቅናቄው አባል ድርጅችና ከሌሎች ምንጮች ማሰባሰብ፤ በሥራ ላይ ማዋል፣
4. ለብሔራዊ አንድነት፤ ለእኩልነትና ለዴሞክራሲ የሚደረገው ሁለ ግብ ትግል ለማጎልበት የተቀናጀ የውጭ ግኑኙነትና የዲፕሎማሲ ተግባሮችን ማከናወን፡
5. የጥምረቱን ድርጅታዊ መዋቅሮች፣ ተግባሮችና ሃላፊነቶች ማዘጋጀት፤ ተግባራዊነታቸውን ማረጋገጥ፤
6. ከየፖለቲካ ድርጅቶቹ የሚወክሉ አባላትን በጥምረቱ ድርጅታዊ መዋቅሮች ውስጥ መመደብ፣ እንቅስቃሴያቸውን ማስተባበር፣ መከታተልና መቆጣጠር፤
7. የጥምረቱን መመዘኛዎች የሚያሟሉ የፖለቲካ ሃይሎች የጥምረቱ አባል እንዲሆኑ አስፈላጊውን ሁሉ ማድረግ፤
8. ጥምረቱ በሂደት ወደ አንድ ወጥ ውህድ የፖለቲካ ኃይል የሚሸጋገርበትን ሁኔታ ማመቻቸትና ተግባራዊ ማድርግ፤

## የድርጅቶች ዝርዝር

1. የአፋር ሕዝብ ፓርቲ
2. ግንቦት 7 የነጻነት የፍትህና የእኩልነት ንቅናቄ
3. የኢትዮጵያ ሕዝብ የአንድነትና የፍትህ ንቅናቄ